# እኛ ሕብረት ስንል ፤ እነሱ ሕብረት ሲሉ

ከአይምሮ ዳኛቸው

ከካቻምናው ያምናው ፤ ካምናው የዘንድሮው እንዲያም እያለ ከቀን ወደቀን የሐገራችን ሕልውና አስጊ ወደሆነ ደረጃ እየተዳረሰ የመጣው ከኛ አንድነት እና ሕብረት ጉድለት የተነሳ እንደሆነ ከማናችንም የተሰወረ አይደለም ። ታዲያ ለዚህ መፍትሄ ለማግኘት የግድ ሕብረት ያስፈልጋል ፤ ይህ ሕብረት እንዳይፈጠር ደግሞ አንዳንድ እንቅፋት የሆኑ ምክንያቶች አሉ ፤ ታዲያ እነዚህ እንቅፋቶች ምንድናቸው? ብሎ መመርመርና መጠየቅ የግድ ይላል ። በኔ ግንዛቤ ለሕብረታችን እንቅፋት ሆነዋል የምላቸውን ምክንያቶች በቅድሚያ በመመልከት አያይዤም መፍትሄ ሊሆን ይችላል ያልኩትን ሃሳብ ለማቅረብ እሞክራለሁ።

ሕብረት ለመፍጠር እንቅፋት ሆኗል ብዬ ከማምንባቸው ምክንያቶች ሁሉ አበይትና ትልቅ ምክንያት ነው የምለው "በራስ አለመተማመን" የቀዳሚነት ስፍራን ይዞ አገኘቼዋለሁ ። ይኸውም ማንኛውም የተቃዋሚ ድርጅት የተነሳበትን የግሉን አላማ ትክክለኛ የፖለቲካ አካሄድ እንደሆነ ቢያምንም ፤ ከሌሎች ተቃዋሚዎችም በላይ በርካታ ደጋፊ አለኝ ብሎ ቢገምትም ፤ ነገር ግን አመራሩም ሆነ ተከታዮቹ ከልብ የተቀበሉት ፤ ሆኖም ግን በማናቸውም የእርከን ደረጃም ከተራ አባላት እስከ አመራር በግልጽ የማይወያዩበትና የማይነጋገሩበት ፤ በውስጠ ታዋቂነት ተቀባይነትን ያገኘ በራስ ያለመተማመን ነግሦና አሽመድምዶ የያዛቸው ስለሆኑ ፤ የሌሎች ሀሳብና አመለካከት ይበልጠናል ብለው ስለሚያምኑ ፤ በሕዝብም ዘንድ ከኛ በተሻለ ተቀባይነት ሊያገኙ ይችላሉ ብለው የደመደሙ ፤ እራሳቸውን አሳንሰውና አኮስሰው በመመልከት የህሊና ትንሽነትና ድክመት አይሎባቸው ሳይታገሉ የተሸነፉ በመሆናቸው ፤ ይህ ደካማ ዕምነታቸው ከገቢራዊው ዓለም እጅግ ለይቷቸው በውስጣቸው ተቀብለውት ነገር ግን አደባባይ አውጥተው የማይናገሩት ድርጅትንና ቡድንን እየፈሩ ፤ እየሸሹ ፤ ስለሚኖሩ ሳይወዱ በግድ ለተዛባ እምነታቸው የፍርሃት ተገዢ ሆነው በመገኘታቸው አንድነትና ሕብረት መመስረት አልተቻለም ።

አንደኛው ድርጅት ወይንም ቡድን ሌላውን ለምን ይፈራዋል ብሎ መጠየቅም አግባብነት ያለው ነው ። አንዱ ሌላውን የሚፈራበት ምክንያት ከላይ እንደ ጠቀስኩት አንድም በራሱ እምነትና አሰራር ላይ ድክመት እንዳለ ስለሚያምንና ተከራክሮም እረታለሁ የሚል እምነት ስለሚጎድለው ሲሆን ፤ ሁለተኛውና ዋነኛው ምንም እንኳን ለአገርና ለወገን ተቆርቋሪ ነን ፤ ትግላችን ሕዝብን ስልጣን ለማስያዝ እንጂ እኛ በግል ስልጣን የመያዝ አላማ የለንም ብለው ቢሰብኩም ፤ እውነታውና ሃቁ ግን ሕዝብን የስልጣን ባለቤት ማድረጉ ሳይሆን እነሱ እራሳቸውን የስልጣን ባለቤት ማድረግ ስለሚፈልጉ ፤ ያ ያላቸው የስልጣን ጥምና ጉጉት ደግሞ በራሳቸው አለመተማመን ክፉኛ የተበረዘ በመሆኑ ፤ ሕብረት በመፍጠሩ ብቻ ከነሱ አስተሳሰብና አሰራር የበለጠና የተሻለ ግለሰቦችንና ቡድኖችን ያመጣል ወንም ያሰባስባል ብለው ስለሚሰጉ ፤ ይህ አስተሳሰባቸው ደግሞ እነሱ ካላቸው የስልጣን ጥማት ጋር እጅግ

በጣም ስለሚቃረን ፤ ባፋቸው የሚናገሩትን በተግባር ለመተግበር ችግር ያለባቸው በመሆናቸው ፤ አፋቸው ከልባዊ ምኞታቸውና ስውር አላማቸው ጋር መራመድ ስለማይችል ፤ ሕብረቱ እንዳይፈጠር የችግሩ ምክንያት ሌሎችን በማድረግና ጣት በመቀሰር ፤ በማጥላላት ፤ ሥም በመስጠት ፤ የምዬን ወዳብዬ በማድረግ ፤ ሌሎች ወገኖች ለሕብረትና ለአንድነት እንቅፋት እንደሆኑ አስመስሎ የሌለ ታሪክ በመዘባረቅና አሉባልታ በመንዛት ፤ በተግባር ጸረ ሕብረት እንቅስቃሴን እያራመዱ ባፋቸው ሕብረትን መስበኩ ሞያ አድርገው ስለወሰዱት ነው ።

ይህንን ዳካማ ጎናቸውንና አድራጎታቸውን እነሱ እራሳቸውን ከሚያውቁት በላይ የአገራችን ጠላቶች የሆኑት ባዕዳንና በስልጣን ላይ ያለውም የጎጠኞቹ አገዛዝ ጠንቅቀው ስለሚያውቁት ይህን የደካሞች ፖለቲካ ማራመድ ይችሉ ዘንድ አስፈላጊውን የገንዘብ ፤ የቁሳቁስና የመሳሰሉትን ድጋፎች በውስጥ አርበኞች አማካኝነት እያበረከቱላቸው ስራ ላይ እንዲውል በማድረግ የሕዝብ ፍላጎትና ምኞት በተፈለገው ሰዓትና ፍጥነት ሥራ ላይ እንዳይውል አስችሏል ።

ይህ ግምጋሜ እንዲያው በደፈናው ካየር ላይ ተቧጦ የመጣ ሳይሆን ሁላችንም እያየነው አላየንም ብለን የምንክደውና የምንሸሸው ፤ ያፈጠጠና ያገጠጠ እውነታ ነው ። እነዚህ ተቃዋሚ ነን ሕብረት ያስፈልገናል ነገር ግን ይሄኛው ወይንም ያኛው ቡድን ለሕብረት መፈጠሩ እንቅፋት ሆኑብን ሲሉ የሚደመጡት ፤ ሆኖም ግን የሚወነጅሉትን አካል ወይንም ቡድን በማናቸውም መድረክ ተገናኝተውት መሟገት የማይችሉ ደካሞች ፤ ነገር ግን ጓሮ ጓሮውን እየዞሩ ስም በመስጠትና ሥም በማጥፋት የተሰማሩ ለሕብረትና ለአንድነት እንቅፋት የሆኑ ትንሽነት በውስጣቸው ነግሶ የሚያሰቃያቸው የሚቃወሙትን ድርጅት ወይንም ግለሰብ በሌለበትና እራሱን መከላከል በማይችልበት መድረክ እየዞሩ የፈጠራ ክስ የሚደረድሩ አሉባልታና ወሬ የተካኑ የሕብረትና የአንድነት እንቅፋት ሆነው ሕብረትና አንድነት እያሉ መዘመር የሚያዘወትሩ አስይ መሲሆች ናቸው ።

ይፈጠር የሚሉትም ሕብረትና አንድነት ዘወትር በወያኔ ዙሪያ ያኮበኮበ ፤ ወያኔን የግድ ማካተት አለበት የሚሉ ፤ በጽናት የወያኔን ሕገመንግስትና ስርአት ለመምታትና ለማፍረስ ፍላጎቱ የሌላቸውና በዚሁ ጸረ ሕዝብና ጸረ አንድነት በሆነ ሕገመንግስት ዙሪያ እንኮልኮል የሚሉ አጎብዳጅ እንጂ ታጋይ ባለመሆናቸው የተነሳ ነው ።

እንዲሁም ሊቀርቧቸውና ሊጎዳኟቸው የሚፈልጉት ወያኔ ሰራሽ የሆኑ ድርጅቶችና ቡድኖችን ፤ ወይንም በወያኔ ስር የተኮለኮሉና ወያኔ አስነጠሰ ብለው ብርክ የሚይዛቸውን ፤ "ከእጅ አይሻል ዶማ" የሆኑትን እንጂ ፤ ኢትዮጵያዊ አጀንዳ ያነገበውን ሊቀርቡም ሊያነሱም ፍላጎቱ የላቸውም ።  ይባስ ብሎም ኢትዮጵያዊ አጀንዳ የሌላቸውን ሽምድምዶችን ደጅ ሲጠኑ ይስተዋላል ።

ይህ በእንዲህ እያለ አሁን ባለንበት ሁኔታ ሕብረት ማድረግ ይቻላል ወይስ አይቻልም? ብሎ ለሚጠይቅ ፤ መልሱ ይቻላል ሲሆን ፤ ይህንን ለማስቻል ግን አሁንም አንዱ ሌላውን በመወንጀል ሳይሆን ሁሉም ተቃዋሚ ነኝ የሚለው ሁሉ በአንድ ላይ በመምጣት እስከ አሁን ለሕብረቱ አለመፈጠር ምክንያት ነበር የሚሉትን አንድም ወደኋላ ሳይሸሹ ፍርጥርጥ አድርጎ ታዛቢ ባለበት ማቅረብ የሚቻልበትና ፤ ጥያቄና መልስ ያለ ተጽእኖ የሚስተናገድበት መድረክ መፍጠር ከተቻለ ሕብረቱን መፍጠር የማይቻልበት ምንም ምክንያት አይኖርም ። ይህ ግቡን እንዲመታ ግን የሁሉንም መልካም ፈቃደኝነትና ተሳትፎን ይጠይቃል።

ዛሬ ሀሐገራችን ያለው የጎጠኛ አገዛዝ ለባዕዳን አጎብዳጅና የባዕዳንን ጥቅም አስጠባቂ በመሆኑ በአሁኑ ሰዓት የምንታገለው በሐገራችን ያለውን የጠባብ ጎጠኞችን አገዛዝ ብቻ ሳይሆን ጥቅማቸውን የሚያስጠብቅላቸውን የባዕዳን ኃይልንም ያካተተ መሆኑን በቅድሚያ ማወቅና መረዳትም የግድ ይላል ።

ይህ ክስተት ትግላችን ሁለት ዘርፍ ያለው እንዲሆን ያደርገዋል ማለት ነው ፤ ይህም ማለት እኛ በተጎሳበትንና በተጠናከርን ቁጥር ባዕዳን የጥቅማቸው ሁኔታ ያሳስባቸዋል ፤ የወያኔም አገዛዝ የነዚሁ ባዕዳን ጥቅም አስጠባቂ በመሆኑ የተነሳ አሁን ያለው አገዛዝ እንዳይወድቅ ፤ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ ባዕዳኑ ለድል እንዳንበቃ የተቻላቸውን ሁሉ በማድረግ ወያኔን ማጠናከራቸውን በሰፊ ሁኔታ ይቀጥሉበታል ። ለዚያም ወያኔ ሰፊ የሆነ የገንዘብ ፤ የቁሳቁስና የስለላ እርዳታዎች ይጎርፉለታል ፤ በውስጣችን ሸርሻሪዎች ሰርገው እንዲገቡና በሐገር ቤትም ሆነ በዲያስፖራው አለመተማመንና ድክመት እንዲፈጠር ከወያኔ ጋር በመመሳጠር ባልተቆጠበ ጥረት ይፈታተኑናል ። ይህ ሁኔታም በሐገር ቤትም ሆነ በውጪው ዓለም ለምናደርገው እንቅስቃሴ አስፈላጊውን ተጽዕኖ ስለሚያደርግ ትግልችንንና ሕብረት ለመፍጠር የምናደርገውን ውጣ ውረድ በአያሌው ወደኋላ ይገታዋል ።

ይህም ሊሆን የሚችልበት ዋናውና ቀዳሚው ምክንያት በዓላማና በአሰራር የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ አለመቻላችን ይሆናል ። በጋራ መሰረታዊ አንድነት ለመፍጠር አሁን ያለውን አገዛዝ መጥላትና እሱን ከማስወገድ ፍላጎት ላይ ብቻ የተመሰረተ አሰራር ደግሞ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እንደሚያመዝን ከምርጫ 97 በሰፊው ትምህርት አግኝተናል ።

የምርጫ 97 ስብስብና አንድነት አሁን በስልጣን ላይ ያለውን አገዛዝ ከመጥላት የመጣ እንጂ በምንም አይነት መልኩ የጋራ የሆነ ሁሉንም ሊያስማማና አብሮ ለመስራት የሚያስችል መሰረታዊ አንድነት እንዳልነበረው በሰፊው ያየነው በመሆኑ ተመልሰን የቀድሞውን ስህተት መድገም አይኖርብንም ። የሚፈጠረው ሕብረት ከወያኔ መወገድ ባሻገር ማየትና ከዚም በኋላ በአንድነት ለመስራት የሚያስችል መተሳሰርን የሚያስችል መሆን ይኖርበታል ።

አንድነትና ሕብረት ከመፍጠራችን በፊት በመጀመሪያ አንድ ሊያደርጉን የሚችሉትን መሰረታዊ እምነቶች እንዳሉ ሆነው በዋነኛነት አንድ ላይ ለመስራት ያላስቻሉንን ሁኔታዎች በዝርዝር ማስቀመጥና እነዚህ ልዩነቶቻችን በማሸጋሸግና አንድ የጋራ የሆነ መሰረታዊ ቅርርብ

EthioLion.com

ማድረግ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ በሰፊው መስራትና ለማቻቻልም መልካም ፈቃደኝነት መኖር ይኖርበታል ። ይህም ፈቃደኝነት በግፊት ሳይሆን ከራስ በመነጨ አነሳሽነት ከምናደርገው ጥረት የተወለደ መሆን ይኖርበታል ።

ይህንንም ፈቃደኝነት የሚያረጋግጠው እንደቀድሞው እኛን የመሰሉንንና እኛ የተናገርነውን እንደ እስፖንጅ ጠጥተው የሚሄዱ ፤ ወይንም እኛን የሚመስሉ መድረኮችና ሚዲያዎች ላይ ብቻ መቅረቡና የተመቻቸ ጥያቄና መልስ ሰጥቶ መሄዱን ማቆም ይኖርብናል ። መልካም ፈቃደኝነቱ ካለ ጠንከር ያለና ለዘላቂ አንድነትና ብሩህ እራእይ ሊያስጨብጡን የሚችሉ ከኛ አስተሳሰብና አመለካከት ትንሽ ለየት ያለ አመለካከት ያላቸው መድረኮችና ሚዲያዎች እየቀረቡ ለሚሰነዘሩ ጥያቄዎች አግባብነት ያላቸው መልሶችን መስጠት ይጠየቅብናል ።

ስለሆነም ለሐገር አንድነትና ሉአላዊነት ተቆርቋሪ ነን የሚል ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት አመራሮች በአሰራራቸው እምነትና ጥንካሬ ካላቸው በተጠሩበት ሚዲያና መድረኮች በመቅረብ የሕዝብን አስተያየትና ጥያቄዎች መቀበል የግድ ይላል ። የናቴ መቀነት አደናቀፈኝ እያሉና ምክንያት እየደረደሩ ለሚደረግላቸው ሕዝባዊ ጥሪ መሸሽ ያረጀና ያፈጀ የተቃጠለ ፊልም ፤ አሊያም የተበላ እቁብ መሆኑን አምነውና ተቀብለው ለሕዝብ ጩኸት መልስ መስጠት ግዴታቸው መሆኑን ማወቅና መረዳት የግድ ይላል ። ይህንን ማድረግ ከተቻለ ትግላችንን ወደተሻለ ምዕራፍ ልናሸጋግረው እንደምንችል ከማንም የተሰወረ አይሆንም ።

ስለሆነም እኛ ሕብረት ስንል ፤ እነሱ ሕብረት ሲሉ የሚለው አባባል መቆምና ወደአንድ ክብ ጠረጴዛ መምጣት ይኖርብናል ። ይህንንም እውን ለማድረግ አሁን በተቃዋሚነት የተሰለፉት አመራሮች አሰራራቸውንም ሆነ አመለካከታቸውን የፖለቲካ ፕርግራማቸውን በመመርኮዝ በቅንነት ለመንቀፍም ሆነ ለመነቀፍ ሁልግዜም ዝግጁ መሆናቸውን ማብሰርና በተጋበዙበት ኢትዮጵያዊ መድረክ ሁሉ ያለምንም ማወላዳት ቀርበው መወያየት ይኖርባቸዋል ።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!

EthioLion.com